# ፖሊሲ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

***ተዛማጅ ምንጮች፡*** EHA, IEE, IFB-RA, IKA, IKA-RA, IOA-RA, JOA-RA
***ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፡*** Instruction and Program Development

# የባለተሰጥኦና የላቀ ችሎታ ትምህርት

**A. ዓላማ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለባለተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ ትምህርት ቅድሚያ የሚሰጥ መሆኑን ማረጋገጥ

አጠቃላይ የአካዳሚክ ፕሮግራሙን ማፋጠን እና ማበልጸግ ተገቢ መሆኑን ማረጋገጥ

ከፍተኛ ውጤት የሚያስገኙ እና ከፍተኛ ውጤት ሊያስገኙ የሚችሉ ተማሪዎችን የግንዛቤ እና ተፅእኖ ፈጣሪ ፍላጎቶችን ለመፍታት ልዩ ትኩረት ለሚሰጡ ሰራተኞች እና ለማህበረሰቡ አቅጣጫ ለመስጠት

የእያንዳንዱን ልጅ የአዕምሮ ችሎታ አድማስ ለማስፋት እና ሁሉም ተማሪዎች አቅማቸውን በከፍተኛ ደረጃ እንዲያሳኩ ለመርዳት

ልዩ የትምህርት ፕሮግራሞች እና/ወይም አገልግሎቶች በሁሉም K-12 ክፍል ለሚማሩ ተሰጥኦ ያላቸው እና ጎበዝ ተማሪዎች፣ ከፍተኛ ችሎታና ተሰጥኦ ያላቸው የአካል ጉዳተኝነት ያላቸው ተማሪዎችን ወይም ሌሎች ልዩ ፍላጎቶችን ጨምሮ ተገቢ አገልግሎት መሰጠቱን ለማረጋገጥ እና በእያንዳንዱ ትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ ያለው የትምህርት አሰጣጥ ተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች የመማር ችሎታቸውን የሚመጥን ተገቢ ትምህርት እንደሚያገኙ ማረጋገጥ።

**B. ጉዳዩ**

ለእያንዳንዱ ተማሪ ስኬት የሚጀምረው ከተማሪ የሚጠበቁ ውጤቶችን በግልጽ በማስቀመጥ፣ የሚጠበቅባቸውን ውጤቶች የማያሳኩ ተማሪዎችን በመለየት፣ የእያንዳንዱን ተማሪ አፈጻጸም ለማሻሻል ተገቢ በሆኑ ስልቶች ጣልቃ በመግባት እና ውጤቶችን በመከታተል ነው። በትምህርት ቤቶቻችን እና ማህበረሰባችን ውስጥ ልዩ ችሎታ እና ተሰጥኦ ያላቸው ልጆች የማህበራዊ ገፅታችን አካል ናቸው። በፍጥነት እና በጥልቀት ትምህርት የመቅሰም ችሎታቸው ከብዙዎቹ ተመሳሳይ የዕድሜ እኩዮቻቸው የሚለያቸው ተሰጥኦአቸው ነው። በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት የመቅሰም አቅም ስላላቸው እና ከእድሜያቸው እኩዮች ጋር ሲነፃፀሩ ልዩ የሆነ ችሎታ እና የመማር ዘይቤ ፍላጎት ስላላቸው፣ እነርሱን በሚመጥን ፍላጎቶቻቸው እና በተለምዶ በሚሰጡት የትምህርት አሰጣጥ መካከል የጎላ ልዩነት ስላለ ያላቸውን ችሎታና ተሰጥኦ በሚመጥን ደረጃ የተሻሻለ የትምህርት እና የስርአተ ትምህርት ማስተካከያ ያስፈልጋቸዋል። ሰፊ ችሎታና ተሰጥኦ የሚያሳዩ እና ከፍተኛ ውጤት ያላቸው እና ከፍተኛ ውጤት ሊያገኙ የሚችሉ ተማሪዎችን ፍላጎት ለማሟላት ልዩ እና ወሳኝ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። ተሰጥኦ ያላቸው እና ጎበዝ ተማሪዎችን በመደበኛ ክፍል ውስጥም ሆነ በልዩ ፕሮግራሞች የሚያስተምሩ ሰራተኞችን መምረጥ፣ ማሰልጠን፣ ሙያቸውን ማዳበር እና መገምገም የእነዚህን ተማሪዎች ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት በሚደረገው ጥረት ወሳኝነት አለው።

C. አቋም

1. ትርጉም፥ ፍቺ

a) ባለ ተሰጥኦ እና ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች በዚህ መመሪያ ውስጥ እንደሚከተለው ተገልጸዋል፦

(1) ከሌሎች በእድሜ፣ በልምድ ወይም ሁኔታ ጋር ሲነፃፀሩ የሚያከናውኑት ወይም በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት የመቅሰም አቅምን የሚያሳዩ ምርጥ ተሰጥኦ ያላቸው ልጆች እና ወጣቶች (እነዚህ ተሰጥኦዎች በሁሉም የኢኮኖሚ ደረጃዎች እና በሁሉም የሰው ልጆች ጥረት፣ ባህል እና ማህበረሰብ ውስጥ ካሉ ህጻናት እና ወጣቶች ላይ የሚገኙ ናቸው።)

(2) በአእምሯዊ፣ በፈጠራ እና/ወይም ስነ ጥበባዊ የትምህርት ስራዎች ከፍተኛ የአፈጻጸም ችሎታ ያላቸው፣ ልዩ የሆነ የመሪነት አቅም ያላቸው ወይም በልዩ የትምህርት ዘርፎች የላቀ ችሎታ ያላቸው ልጆች እና ወጣቶች (በትምህርት ቤቶች ውስጥ በተለምዶ ከሚቀርቡት ትምህርቶች በላይ ሊሆኑ የሚችሉ የትምህርት አገልግሎቶችን ወይም አክቲቪቲዎችን ይፈልጋሉ)

b) ትምህርትን ማፋጠን ማለት ለተማሪዎች ከመደበኛው ሥርዓተ ትምህርት የበለጠ ደረጃ ያለው ሥርዓተ ትምህርት መስጠት ነው፤ የትምህርቱ ይዘት የበለጠ መረጃ ያለውና የተወሳሰበ ከፍተኛ ችሎታን የሚጠይቅ ሲሆን፥ የመማሪያ ቁሳቁሱ ከተለመደው መማሪያ በበለጠ ፍጥነት የሚሠራ፣ እና ተማሪዎች በክፍል ደረጃ ከተለመደው ቁሳቁስ የበለጠ ጥረት ማድረግ ይገጥማቸዋል። በዚህ ብቻ ባይወሰንም ከፍ ያለ የተፋጠነ ትምህርት ሲባል የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፦

(1) በአንድ የትምህርት አይነት የላቀ ምደባ (ተማሪ ወደ ቀጣዩ ከፍተኛ ክፍል ሳይ(ት)ዘወር፣ ተማሪው(ዋ) ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ የትምህርት ዓይነቶች በላቀ የክፍል ደረጃዎች ካሉ ተማሪዎች ጋር ለግማሽ ቀን እንዲማሩ ይመደባሉ)

(2) ስርአተ ትምህርቱን ማጠቃለል (ትምህርቱ ተጠቃሎ የተቀነሰው ጊዜ ተማሪው(ዋ) በስርአተ ትምህርቱ በፍጥነት ለመገስገስ የሚያስችል መግቢያ፣ ትግበራዎች፣ ልምምድ፣ ክለሳ እና ግምገማ ይሰጣል)

(3) ሥርዓተ ትምህርት ቴሌስኮፒንግ (ተማሪው(ዋ) በኮርስ ጥናት ላይ ከወትሮው ያነሰ ጊዜ ያሳልፋል/ታሳልፋለች፤ ለምሳሌ፦ በአንድ ሴሚስተር የአንድ ዓመት ኮርስ ያጠናቅቃል/ታጠናቅቃለች)

(4) በአንደኛ ደረጃ/በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በመካከለኛ/በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/በኮሌጅ ውስጥ አንድ ላይ የተሳለጠ ፕሮግራም ማውጣት

c) ማበልጸግ ተማሪዎች በጥልቀት እና በስፋት እንዲማሩ እድል መስጠት ተብሎ ይገለጻል። ማበልጸግ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም፦

(1) ተማሪዎች የሚያዘነብሉትን ትምህርት ይዘት በጥልቀት በመመርመር እና በመተንተን ምርጫ ማድረግ የሚያስችላቸው የይዘት ውስብስብነት ነው

(2) ንጽጽሮችን እና እያወዳደሩ ማገናዘብን የሚፈልግ እና የተገኘውን መረጃ በተግባራዊ እና ዕውቀትን በሚቀይሩ መንገዶች መጠቀምን በሚያበረታታ ማሰብ ላይ አጽንዖት ይሰጣል

(3) ከጥልቅ እውቀት እና ነጸብራቅ (ትንተና) የተገኙ የፈጠራ እና የመጀመሪያ ውጤቶች

2. ስርአተ ትምህርት

a) ከቅድመ-መዋዕለ ህፃናት እስከ 8ኛ ክፍል፣የተፋጠነ እና የዳበረ ስርአተ ትምህርት የዚህን ፕሮግራም ፈተና ለመውሰድ አቅም ወይም ዝንባሌና ተነሳሽነት ላላቸው ለሁሉም ተማሪዎች ይሰጣል። ይህ ሥርዓተ ትምህርት ጥብቅ እና ፈታኝ ከመሆኑም በላይ ትምህርት የመቅሰም ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ችሎታ፣ የስኬት ደረጃ እና ፍላጎት ጋር የሚጣጣም ይሆናል።

b) ተማሪዎች በተፋጠነ ሁኔታ እንዲማሩ፣ በጥልቀት እንዲማሩ እና በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች መካከል የተቀናጁ ጭብጦችን እና ግንኙነቶችን እንዲማሩ ተማሪዎች ከፍተኛውን የአካዳሚክ ትምህርት ደረጃ እንዲደርሱ እድሎች እና የሚጠበቅባቸው ተግባሮች ይኖራሉ።

(1) ተማሪዎች አስቀድመው የሚያውቁትን ለመወሰን የሚደረገው ግምገማ በሁሉም የስርዓተ ትምህርት ዘርፎች የላቀ ትምህርት ለማዘጋጀት በተከታታይ ጥቅም ላይ ይውላል።

(2) የትምህርት ፍጥነትን ለማመጣጠን እና የትምህርት አሰጣጥን ሚዛን ለመጠበቅ መጠየቅ፣ የአነስተኛ ቡድን ወይም የግለሰብ ምክክር፣ ችግር ፈቺ እና ከፍተኛ ደረጃ ጥያቄን የሚያካትቱ የማስተማሪያ ስልቶችን በመጠቀም መካከል ማመዛዘን ይኖራል። ሥርዓተ ትምህርቱ ለተማሪ ጥንካሬዎች እና ፍላጎቶች ምላሽ ከመስጠት አኳያ የሚመቻች ይሆናል።

(3) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ዓላማዎች እና የእንቅስቃሴዎች መጠነ ስፋት እና ቅደም ተከተል እንዲሁም መደበኛውን ሥርዓተ ትምህርት የሚያፋጥኑ እና የሚያበለጽጉ ቁሳቁሶችን ያዘጋጃሉ፣ ከቅድመ መዋዕለ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል በሂሳብ፣ በንባብ/የቋንቋ ስነጥበብ፣ ሳይንስ እና ሶሻል ሳይንስ ተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች በተገቢው የዳበረ እና ከተማሪ ስኬት እና ዝግጁነት ጋር በሚመጣጠን ፍጥነት እንዲራመዱ የሚያስችል ትምህርት ያዘጋጃል።

(4) መምህራን ከመደበኛ መጽሐፎች በተጨማሪ ተገቢ የሆኑ ከክፍል ደረጃ በላይ የሆኑ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፥ ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም።

c) የሥርዓተ ትምህርት ደረጃው ፖሊሲው ከፀደቀ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የመጀመሪያ ቅርጸት ይዘጋጃል፣ እነዚህ ደረጃዎች በጊዜ ሂደት ይሻሻላሉ ወይም ክለሳ ይደረጋል ተብሎ ይጠበቃል። እነዚህ መመዘኛዎች የሚዘጋጁት ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች የሚገዳደር ሥርዓተ ትምህርት እና የግምገማ ልምዶችን ለማረጋገጥ ነው። የተማሪ የትምህርት እድገትን መገምገም፥ የትምህርት ይዘት እውቀትን እና ከፍተኛ ደረጃ የአስተሳሰብ ችሎታ ማሳየትን ይጨምራል። የግምገማ እርምጃዎቹ ለከፍተኛ ስኬት መለኪያዎችን በግልፅ ያሳያሉ።

d) በሁሉም ትምህርት ቤቶች ከመዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ስርአተ ትምህርትን ለማዳረስ የተለያዩ ድርጅታዊ አማራጮች ይተገበራሉ።

(1) የተማሪዎቹ ዝንባሌ እና የጥናት ርእስ ፍላጎታቸውና ችሎታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በሁሉም የማስተማር ደረጃዎች የተስፋፋ፣ ሰፊና ጥልቅ በአጭር ጊዜ የሚጠናቀቅ ከበድ ያለ ስራ፣ የዳበረ፣ እና የተፋጠነ ስርአተ ትምህርት በሁሉም ትምህርት ቤቶች ለመስጠት እንደአመቺነቱ የተለያዩ በቡድን የሚሠሩ ተግባሮችን ይጠቀማሉ።

(2) ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች እንደትምህርቱ ይዘት መጠን ተመሳሳይ ችሎታ ካላቸው ቡድኖች፣ እንደየችሎታቸው የተለያዩ ቡድኖች እና በተናጥል የመስራት እድል እንዲኖራቸው ሚዛን መጠበቅ ያስፈልጋል።

e) ትምህርት ቤቶች ከፍተኛ ደረጃ ችሎታ ያላቸው ልጆች ከሌሎቹ እንዳይገለሉ የሚያረጋግጡበት የክፍል ስራዎችን ይሰጧቸዋል።

3. ፕሮግራም።

ባለ ተሰጥኦ እና ጎበዝ ተማሪዎች መካከል ያለውን የተለያየ የፍላጎት እና የችሎታ መጠን ምላሽ ለመስጠት፣ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ለባለተሰጥኦ እና ጎበዝ ተማሪዎች ተገቢ፣ እና በግልፅ የተቀመጠ ፕሮግራም ይኖረዋል።

a) ከመዋእለ ህጻናት እስከ ስምንተኛ ክፍል (K-8) ፕሮግራም እንደ አስፈላጊነቱ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት እና በሌሎች ቅንብሮች/መቼት ይዘጋጃል። ባለተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ ላላቸው የሚዘጋጅ እቅድ የሚከተሉትን ልዩ ዝግጅቶች ያካትታል፦

(1) ፈታኝ የሆነ ጠንካራ ትምህርት፣እንደሁኔታው የሚመቻች ቡድን እና የመርሐግብር ዝግጅቶች የላቀ ችሎታ ያላቸው እኩዮች ጋር በሒሳብ፣ በንባብ/የቋንቋ ስነጥበብ፣ በሳይንስ፣ ማሕበራዊ ጥናት እና በውጭ ቋንቋ ጥልቅ ጥናት ለማድረግ ጊዜ የሚሰጡ ዝግጅቶች

(2) ፕሮግራሙ ከወላጆች ጋር ያለው ግንኙነት

b) የላቀ ችሎታ ፕሮግራም/Honors Program በትምህርት ቤቶች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ከፍተኛ ተሰጥኦ እና የላቀ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎችን ለማገልገል ማስተላለፊያ መንገድ ይሆናል።

c) ከፍተኛ ተሰጥኦ ያላቸው እና የማግኔት ፕሮግራሞችን ጨምሮ የተለየ ፕሮግራም ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ሌሎች ልዩ ፕሮግራሞች በማዕከላት መሰጠታቸው ይቀጥላል፥ እንደ አስፈላጊነቱ አዳዲስ ፕሮግራሞችም ይዘጋጃሉ።

4. መለያ ስልት

a) MCPS 2ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች ሁሉ ሰፋ ያለ የመለያ ስልቶችን የሚጠቀም ከመሆኑም በላይ በአንደኛ ደረጃ ክፍሎች የሚማሩ ተማሪዎችን ዳግመኛ የማጣራት ስራ ይሰራል። በባለ ተሰጥኦ እና ጎበዝ ተማሪዎች መካከል የተለያዩ ችሎታዎች እንዳሉ በመገንዘብ ይህ የምልመላ ሂደት ብዙ የአካዳሚክ እና የአመራር እምቅ አቅምን በመጠቀም የአካዳሚክ ውጤት፣ ብቃት እና ፈጠራ እና ለሌሎች ቋንቋ ተማሪዎች የተነደፉ የፈተና ስልቶችን መጠቀምን ጨምሮ የተማሪ ሥራ ናሙናዎችን፣ እና ከመምህራን፣ ከካውንስለሮች፣ ከእኩዮች፣ ከወላጆች፣ ከትምህርት ባለሙያዎች፣ ከማህበረሰብ አባላት እና ከተማሪዎች ከራሳቸው ባለተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው ጎበዝ ተማሪዎችን የመለየት ሒደት ይከናወናል።

b) ጎበዝ እና ባለተሰጥኦ ተማሪዎችን በሊጋ የልጅነት ዕድሜ ፍላጎታቸውን ለማሟላት፦

(1) ትምህርት ቤቶች ምንባብን እና ሌሎች የአካዳሚክ ፕሮግራሞችን በአግባቡ ለማስተካከል የተማሪዎችን ችሎታ በቅድሚያ ለማወቅ እና ለማበረታታት የተቻለውን

ሁሉ ጥረት ያደርጋሉ።

(2) ቅድመ መዋዕለ ሕፃናት፣ አንደኛ እና ሁለተኛ ክፍል አስተማሪዎች የማወቅ ጉጉት፣ ፈጠራ እና የአስተሳሰብ ክህሎትን የሚያዳብሩ አክቲቪቲዎችን ያቅዳሉ።

c) ትምህርት ቤቶች ከ6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ተማሪዎችን የኮርስ ቅድመ ሁኔታዎችን ካሟሉና ባለፉት ክፍሎች አዳጋች የሆኑ የትምህርት ስራዎችን ለመሥራት ባሳዩት ፍላጎት ላይ በመመሥረት፣ የአስተማሪ ምክሮች ወይም ሌሎች ተገቢ እርምጃዎችን በመጠቀም የላቀ ችሎታ እና ባለተሰጥኦ ፕሮግራም ውስጥ እንዲገቡ ወይም ከፍተኛ ችሎታ እና ባለተሰጥኦ የክላስተር ቡድን ውስጥ እንዲካተቱ ይመለምላሉ።

d) ከ9ኛ እስከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ከፍተኛ የትምህርት ችሎታን ወደሚጠይቅ የላቀ ትምህርት ምደባ የሚገቡት ባለፉት ክፍሎች የኮርስ ቅድመ ሁኔታዎችን በመማር፣ ፈታኝ የሆኑ የትምህርት ስራዎችን ለመጨረስ ባሳዩት ፍላጎት፣ የተማሪ ዝንባሌ፣ የአስተማሪ/የካውንስለር አስተያየቶች ወይም ሌላ ተገቢነት ያላቸው መስፈርቶች ላይ በመመስረት ነው።

5. ትምህርትን የማበልፀግ ሙያዊ ምክር

በቂ ውጤት የሌላቸው እና በተለምዶ አነስተኛ/ዝቅተኛ ውክልና ያላቸው ተማሪዎች በተለያዩ ጥረቶች ትኩረት ይሰጣቸዋል፦

a) በመጀመሪያ ክፍሎቻቸው ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ እና ከፍተኛ ውጤት ሊያስመዘግቡ የሚችሉ ተማሪዎችን መደበኛ ያልሆነ ማጣሪያ ማድረግ

b) የትምህርት አቅማቸውን የማዳበር መንገዶችን ከአስተማሪዎች፣ ከወላጆች እና ከትምህርት አስጠኚዎች ጋር መስራት

c) ተሰጥኦ እና ከፍተኛ የመማር ችሎታ ያላቸው የአካል ጉዳተኞችን እና/ወይም አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ቡድኖችን ባህሪያት እና ለእነዚህ ተማሪዎች ፈታኝ ትምህርት እንዲማሩ የሚያግዙ የማስተካከያ ዘዴዎችን ማሰራጨት

d) ለረጅም ጊዜ ትምህርታዊ እንክብካቤ የሚሰጣቸው ፕሮግራሞችን ማቀድ

6. አስተማሪዎች እና ርእሰ መምህራን ተሰጥኦ ላላቸው ተማሪዎች የተሳካ ትምህርት እንዲያገኙ ለማድረግ እጅግ ጠቀሚ ሚና አላቸው። ተሰጥኦ ባላቸው ተማሪዎች ተፈጥሮ እና ፍላጎቶች ላይ የተሟላ ስልጠና፣ ተገቢ የማስተማሪያ ስልቶችን እና የፕሮግራም ልምዶችን እንዲሁም ባህሪያት መለያዎችን እና የፕሮግራም አወጣጥ ስልቶችን እና ኅበዝ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን አኮሞዴሽን አስፈላጊነትን ጨምሮ አጽንኦት መስጠት አስፈላጊ ነው። ከግንዛቤ ማስጨበጥ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የክህሎት ደረጃ ያለው የሰራተኞች የሙያ ማዳበር ስልጠናዎች ቀጣይነት ባለው መልኩ ይሰጣሉ።

7. ግንኙነት

የሚከተሉትን የሚያካትት የግንኙነት ስርዓት ይኖራል፦

a) ስለ ባለተሰጥኦ እና የላቀ ችሎታ ፕሮግራሞች ይዘት እና ከተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን የትምህርት ውጤት ለወላጆች ማሳወቅ፣ ስለ ምልመላ ሂደቶች፣ በድጋፍ እና አቀንቃኝ ቡድኖች

በኩል ስለሚገኙ አገልግሎቶች ማሳወቅ

b) ስለ ትምህርት ክንውን ደረጃዎች፣ ከፍተኛ ውጤት ላመጡ እና ከፍተኛ ውጤት ሊያመጡ ስለሚችሉት ተማሪዎች ትክክለኛ ግምገማዎችን እና የልጃቸውን የትምህርት እድገት በሚመለከት ለወላጆች ሪፖርት ማድረግ

c) በትምህርት ቤት ውስጥ ስለ አንድ ተማሪ ፕሮግራም የሚመለከቱ ጉዳዮችን ርእሰ መምህር እና አስተማሪ ከወላጅ ወይም አሳዳጊ ጋር በመደበኛው የምክክር ሂደት መፍታት። ያልተፈቱ ጉዳዮች በሌሎች አስተዳደራዊ ሂደቶች፣ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ የትምህርት አመራር ቡድንን ጨምሮ በጊዜው እንዲስተናገዱ ይደረጋል።

d) ስለ ባለተሰጥኦ እና የላቀ ጉብዝና ያላቸው ተማሪዎች ፕሮግራሞች፣ እድሎች እና ስኬቶች በተገቢው ሁኔታ ለሰፊው ማህበረሰብ ማሳወቅ።

8. ማስተባበር

ባለተሰጥኦ እና የላቀ ጉብዝና ያላቸው ተማሪዎች ፕሮግራሞችን ለመተግበር ማዕከላዊ ማስተባበሪያ የሚከተሉትን የሚያካትት ሲሆን ነገር ግን በዚህ ብቻ አይገደብም፦

a) የእቅድ እና የበጀት ዝግጅት

b) በፕሮግራም ማቀናበር እና ወላጆች ለተማሪ ፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችላቸው ለትምህርት ቤት ሰራተኞች እገዛ እና ድጋፍ መስጠት

c) እንደአስፈላጊነቱ ተሰጥኦ እና የላቀ ጉብዝና ያላቸው ተማሪዎችን የመለየት መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣ መተግበር፣ መከታተል እና ማሻሻል

d) ተሰጥኦ እና የላቀ ጉብዝና ላላቸው ተማሪዎች የስርዓተ ትምህርት ቁሳቁሶችን መምረጥ እና ማዘጋጀት

e) አስተዳዳሪዎችን፣ አስተማሪዎችን፣ ካውንስለሮችን እና የማዕከላዊ ጽህፈት ቤት ሠራተኞችን ጨምሮ ለተለያዩ ታዳሚዎች ስልጠና መንደፍ እና ማሰልጠን

f) ከትምህርት ቤቶች እና ከሰራተኞች አገልግሎት ቢሮ ጋር በመተባበር ለከፍተኛ ተሰጥኦ እና ልዩ ፕሮግራሞች ማዕከላት ሰራተኞችን መምረጥ

g) የፕሮግራም ተሳትፎን ለመከታተል መረጃ መሰብሰብ

D. **የሚፈለጉ ውጤቶች**

1. በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት የተፋጠነ እና የበለፀገ ፕሮግራም በየትምህርት ቤቱ K-12 በመደበኛነት ይሰጣል።

2. እንዲህ ማድረግ የሚችሉ ተማሪዎች በሙሉ ከክፍል ደረጃ በላይ እና በላቁ እና የበለጸጉ ቁሳቁሶች በሁሉም የትምህርት ይዘት ዘርፎች በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ውስጥ በየክፍል ደረጃ እንዲሰሩ እድል ይሰጣቸዋል።

3. ሁሉም ትምህርት ቤቶች የተፋጠነ እና የበለፀገ ትምህርትን የሚያጎለብቱ እንደሁኔታው የሚመቻቹ እና የተለያዩ የቡድን ዝግጅቶችን ይጠቀማሉ።

4. የመማሪያ ክፍል፣ የትምህርት ቤት አደረጃጀት እና የማስተማሪያ ስልቶች የተማሪ አስተዳደግን እንዲሁም ችሎታቸውን እና ፍላጎቶቻቸውን ለማስተናገድ ይዘጋጃሉ።

E. **ተግባራዊ ስልቶች**

ሱፐርኢንተንደንቷ የዚህን ፖሊሲ ትግበራ በቀጥታ እና በተለይም እያንዳንዱ ትምህርት ቤት መስፈርቶቹን የሚያሟላ ፕሮግራም እንዳለው ማረጋገጥ አለባቸው። ሱፐርኢንተንደንቷ ከሚወስዳቸው ልዩ እርምጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

1. በወጥነት መተግበር፣ በየጊዜው መገምገም እና እንደ አስፈላጊነቱ MCPS ከመዋእለ ህፃናት እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል (K-12) የማሰብና የመመራመር አእምሮአዊ ችሎታ/አካዳሚክ ወይም ቪዥዋል እና የአፈጻጸም ስነጥበብ ሥራዎች እና የልዩ እና የማግኔት ፕሮግራሞችን ማዳበር፣ መተግበር እና በየጊዜው መገምገም።

2. የማሰብና የመመራመር አእምሮአዊ ችሎታ/አካዳሚክ እና ቪዡወል እና የአፈጻጸም ስነጥበብ ፈታኝ ስርዓተ-ትምህርትን ማዘጋጀት እና አስፈላጊ ሲሆን ከፍተኛ ደረጃ ያለውን ስርአተ ትምህርት ማሻሻል እና በቀጣይነት እውቀትን የሚያጎለብቱ አላማዎችን ማቅረብ።

3. ለተፋጠነ እና ለበለፀገ ትምህርት ተስማሚ ይዘቶችን በሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስርአተ ትምህርት ሰነዶች ውስጥ ማካተት እና ተጨማሪ የታለሙ የስርዓተ ትምህርት ሰነዶችን እና የመርጃ ቁሳቁሶችን ማቅረብ።

4. እንደአስፈላጊነቱ አዳዲስ ስርአተ ትምህርቶችን ማዘጋጀት እና ተጨማሪ ቁሳቁሶችን በመለየት ያለማቋረጥ መገምገም እና ማሰራጨት

5. ተማሪዎች የመማር ልምዶቻቸውን እንዲያበለጽጉ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚስፋፉ አገልግሎቶችን ማግኘት የሚችሉበት የማስተማሪያ ቴክኖሎጂዎችን ማዳበር

6. በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ የተለያዩ ትምህርታዊ አማራጮችን ማዘጋጀት

7. ስኬታማ ሥርዓተ ትምህርቶችን እና የማስተማር ስልቶችን የላቀ ችሎታ እና ባለተሰጥኦ ፕሮግራሞችን ወደ አጠቃላይ የትምህርት ፕሮግራም ማስተላለፍ

8. መመሪያውን ለመተግበር በቂ ግብዓቶችን የሚያቀርቡ የበጀት ጥያቄዎችን ማዘጋጀት

9. በተለይም በመዋለ ሕጻናት እና በለጋ የልጅነት እድሜ ውስጥ የተለያዩ ተሳትፎዎችን ለማሳደግ እና እምቅ ተሰጥኦዎችን ለማዳበር ውጤታማ ስልቶችን ማሰራጨት

10. አካዳሚክ ቤንችማርኮችን እና ትክክለኛ ግምገማዎችን መተግበር እና በአግባቡ ከፍተኛ አካዴሚያዊ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ስርአተ ትምህርት ውስጥ የተፈለገውን ውጤት የሚለኩበት ዘዴ እና ከእነዚህ ደረጃዎች ጋር በተያያዘ ልጃቸው እንዴት እየሰራ(ች) እንደሆነ ለወላጆች ማሳወቅ፡-

    a) የግምገማ መሳሪያዎቹ ከመመዘኛ ጋር የተገናኙ ፈተናዎችን፣ የማረጋገጫ ዝርዝሮችን፣ ፖርትፎሊዮዎችን፣ አውደርእዮችን፣ ሰርቶ ማሳያዎችን፣ የስራ ምርቶችን እና ዘገባዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

    b) አስፈላጊ ሲሆን፣ እነዚህ ግምገማዎች የመማር/ማስተማር ሂደት ዋና አካል እንዲሆኑ ይዘጋጃሉ፣

እናም ተማሪዎች የእራሳቸውን የትምህርት እድገት እና ውጤት እንዲገመግሙ ትምህርት ይሰጣቸዋል

c) ትምህርት ቤቶች ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ በአመት ሁለት ጊዜ የሚሠራጨውን የተማሪ መገለጫ መሠረት በማድረግ የሥርዓተ ትምህርት ይዘትን፣ ተማሪዎች በክፍል ደረጃቸው የሚጠበቅባቸውን የትምህርት ክንውን እና የአንደኛ ደረጃ ሂሳብን በመከታተል ረገድ በሒሳብ ትምህርት የተማሪ ግስጋሴን (ISM) ለወላጆች/አሳዳጊዎች ሪፖርት በማድረግ ያሳውቃሉ

d) MCPS በየአመቱ አልጀብራ 1 የሚያጠናቅቁ ተማሪዎችን ቁጥር እና በመቶኛ/ፐርሰንት ስለእያንዳንዱ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውጤት ሪፖርት ያደርጋል

e) ትምህርት ቤቶች ከመዋለ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍሎች በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ የበለፀገ እና ፈጣን ትምህርቶች ጋር የሚጣጣም ኅበዝ እና የላቀ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች ቀጣይነት ያለው የግምገማ መስፈርት ይጠቀማሉ። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ መስፈርት የተዘጋጁ ፈተናዎች በየአመቱ ከፍተኛ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች የታወቁ ደረጃዎችን እና የአፈጻጸም መለኪያዎችን በመጠቀም ይካሄዳሉ።

f) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በላቀ ደረጃ ምደባ (AP) ውጤታቸው 3 ወይም ከዚያ በላይ ያገኙ ተማሪዎችን ቁጥር በየዓመቱ ለእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሪፖርት ይደረጋል።

11. ተማሪዎችን በአካዳሚክ ውድድር ላይ እንዲሳተፉ ማበረታታት

F. *ግምገማ እና ሪፖርት*

1. በመጀመሪያዎቹ ሶስት አመታት ውስጥ ይህን መመሪያ በመተግበሩ ሂደት ላይ ለትምህርት ቦርድ አመታዊ ሪፖርት የሚቀርብ ሲሆን አስፈላጊ ከሆነ የመመሪያ ለውጦች እንዲደረጉ ምክረሃሳቦች ይካተታሉ።

2. የባለ ተሰጥኦ እና ከፍተኛ የትምህርት ችሎታ ፖሊሲ የትግበራ ጊዜ ማእቀፍ በየዓመቱ ይዘጋጃል እና ይሻሻላል።

3. በተማሪ ውጤታማነት፣ የፕሮግራም ስኬታማነት ግምገማዎች እና ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች ላይ በመመስረት ይህ ፖሊሲ በትምህርት ቦርድ ፖሊሲ የግምገማ መስፈርት እየተጠበቀ በቀጣይነት ይገመገማል እና ይሻሻላል።

**የዚህ ፖሊሲ ታሪክ፡-** የፀደቀበት ውሳኔ ቁ. 789-78, ኖቬምበር 14, 1978፥ ውሳኔ ቁጥር 518-86 ሴፕቴምበር 22, 1986 ተሻሽሏል፥ በውሳኔ ቁጥር 776-95, ኖቬምበር 14, 1995 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ:- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

<table>
<tr><th>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</th><th>MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</th></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">"Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል:- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር:- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org